# ደንብ

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**

**ተዛማጅ የመረጃ ምንጮች:** COB-RA, COF-RA, IGN, IGO-RA, JPC-RA, JPD-RB
**ኃላፊነት የሚመለከተው ጽ/ቤት:** Office of the School System Medical Officer

## ኦፒዮይድ ከመጠን በላይ ለወሰዱ ግለሰቦች የድንገተኛ ህክምና እርዳታ

I. **ዓላማ**

የኦፒዮይድ-ማስታገሻ መድሐኒቶችን ጨምሮ ኦፒዮይድ ከመጠን በላይ የመውሰድ ምልክቶች ለሚታዩበት ሰው ወይም በተገቢ ሁኔታ ኦፒዮይድ በመውሰድ እየተጎዳ መሆኑ ለሚታመን ማንኛውም ግለሰብ አስቸኳይ የህክምና እርዳታ የመስጠት አሠራር ለመዘርጋት።

MCPS ናሎክሶን ወይም ሌላ ኦፒዮይድ ከመጠን በላይ በመውሰድ ምክንያት የሚያስከትለውን ጉዳት የሚቀለብስ ማስታገሻ መድሃኒት የማግኘትና የማከማቸት፣ እና የተወሰኑ ሰዎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ውስጥ ለተማሪዎች ወይም ለሌሎች ግለሰቦች መድኃኒት መስጠት እንዲችሉ ለማሰልጠን እና ፍቃድ የሚያገኙበትን ሂደት ለመዘርጋት።

II. **ዳራ**

ኦፒዮይድ ከመጠን በላይ መውሰድ እና መሞት በአገር አቀፍ ደረጃ እና በሜሪላንድ ስቴት ውስጥ እንደ ወረርሽኝ ተስፋፍቷል። የሜሪላንድ የጤና ዲፓርትመንት (MDH) እና የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት (MSDE) ለዚህ ወረርሽኝ ምላሽ ለመስጠት ትምህርት ቤቶች እና የት/ቤቶች ጤና አጠባበቅ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የት/ቤት የጤና ጥበቃ አገልግሎት ዲፓርትመንት (SHS) ያላቸውን ሚና ይገነዘባሉ። ከጁላይ 1, 2017 ጀምሮ በሥራ ላይ የዋለው "Start Talking Maryland Act," የተሰኘ የሜሪላንድ ህግ፣ ፐብሊክ ስኩልስ ናሎክሶን ወይም ሌላ ኦፒዮይድ ከመጠን በላይ ለወሰዱት ማስታገሻ መድሃኒት እንዲያገኙ እና እንዲያከማቹ እና የተወሰኑ ሰዎች በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ለተማሪዎች ወይም ለሌሎች ግለሰቦች መድኃኒት መስጠት እንዲችሉ ማሰልጠን እና ፍቃድ እንዲሰጡ ይጠይቃል።

III. **ትርጉም**

A. ኦፒዮይድ ለህመም ማስታገሻ ወይም የተዛባ የኦፒዮይድ አጠቃቀምን ለማከም በህጋዊ መንገድ የሚታዘዙ ኦፒየም ወይም የኦፒየም ተዋጽኦዎች ያሏቸው ንጥረ ነገሮች ናቸው። በተለያዩ ቅርጾች ሊገኙ ይችላሉ፥ እንዲሁም በሕገወጥ መንገድ ተመርተው ያለሐኪም ትእዛዝ ሊሸጡ ይችላሉ።

B. ኦፒዮይድ ከመጠን በላይ መውሰድ የሚያስከትለው መርዛማ የሆነ የኦፒዮይድ መጠን፣ ከሌሎች ንጥረ ነገሮች ጭምር ሲደባለቅ፣ የሰውነትን የማዋሃድ አቅም ያጨናንቃል። ኦፒዮይድ ከመጠን በላይ መውሰድ የመተንፈስ ጭንቀትን ጨምሮ ለሕይወት አስጊ ሁኔታዎችን ሊያስከትል ይችላል።

C. የኦፒዮይድ ማስታገሻ መድሐኒቶች (ለምሳሌ፡- ናሎክሶን/naloxone) ለጊዜው ኦፒዮይድ ከመጠን በላይ መውሰድ የሚያስከትለውን የተበከለ የመተንፈስ አለመቻል ውጥረት ለመቋቋም ይረዳሉ። ምንም እንኳን ኦፐዮይድ ከመጠን በላይ የመውሰድ ምልክት ባይታይም ወይም አንድ ግለሰብ ያላወቀ(ች)ውም ቢሆን

ናሎክሶን የህክምና እርዳታ መስጠት ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑ ይታመናል። አብዛኛውን ጊዜ ናሎክሶን የሚሰጠው ለአንድ ጊዜ ብቻ እንዲጠቅም በአፍንጫ የሚረጭ ሲሆን ነገር ግን በመርፌ በመውጋትም ሊሰጥ ይችላል። ኦፒዮይድ ከመጠን በላይ መውሰድ በትክክል ከተጠረጠረ ናሎክሶን መስጠት አለበት።

IV. **ቅደም-ተከተሎች/ሂደቶች**

A. ስልጠና

1. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤት ሰራተኞች በሙሉ እና ሌሎች የተመደቡ MCPS ሰራተኞች ስለ ኦፒዮይድ ግንዛቤ እና እርምጃ ስለመውሰድ የሚሰጠውን ስልጠና በየአመቱ ማጠናቀቅ ይጠበቅባቸዋል። ስልጠናው "Professional Development Online (PDO)" ድረገጽ ላይ ይገኛል።

2. እያንዳንዱ የትምህርት ቤት ርእሰመምህር ከትምህርት ቤቱ የማህበረሰብ ጤና ነርስ (SCHN) ጋር በመመካከር ስለ ናሎክሰን መድኃኒት አሰጣጥ ተጨማሪ መደበኛ የተግባር ስልጠና እንዲወስዱ ቢያንስ ሶስት የትምህርት ቤት ሰራተኞችን የመለየት ሃላፊነት አለበት።

3. ርዕሰ መምህራን የሚከተሉትን ማድረግ የሚችሉ ሰራተኞችን እንዲለዩ ይበረታታሉ –

   (1) በትምህርት ቤት ስፖንሰር የሚደረጉ እና ከትምህርት በኋላ የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች እና ዝግጅቶች ላይ መሳተፍ የሚችሉ፣ እና

   (2) በተቻለ መጠን የመጀመሪያ እርዳታ ለመስጠት እና ስለልብ አተነፋፈስ የሰለጠኑ። በልብ አተነፋፈስ አስቸኳይ እርዳታ ለመስጠት ሰልጥነው የምስክር ወረቀት ያላቸው ቢሆን ይመረጣራል ነገር ግን ግዴታ መሆን የለበትም።

4. ናሎክሰንን ለመስጠት ሰራተኞች የሚሠለጥኑት በፈቃደኝነት ነው።

5. DHS ወይም MCPS የትምህርት /ቤቶች የጤና አገልግሎት ኃላፊ ለእያንዳንዱ ትምህርት ቤት በተመደበው SCHN ወይም በሌላ ግለሰብ የተግባር ስልጠና ይሰጣል። የሥልጠና ሠነዶች እና የሥልጠና ሪኮርዶች DHHS እና MCPS አሠራር መሠረት በትምህርት ቤት የጤና አገልግሎት ሠራተኞች ይጠበቃሉ።

6. ኦፒዮይድ ከመጠን በላይ የመውሰድ ምልክቶች እና ምልክቶቹን ለይቶ ማወቅ፣ ናሎክሶን በአፍንጫ መስጠት፣ የአደጋ ጊዜ ክትትል ሂደቶች፣ እና የሰነድ አያያዝ መስፈርቶችን እና የሥልጠና ደረጃዎችን ያካትታሉ፣ ነገር ግን በዚህ ብቻ አይገደብም።

B. ናሎክሶን ማስታገሻ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ህንፃዎች ውስጥ ማከማቸት

1. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ "Maryland Overdose Response Program" አማካይነት ከጤና ጥበቃና ሰብአዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት (DHHS) ወይም በቀጥታ ከ "Maryland Overdose Response Program" ናሎክሶን/naloxone ያገኛል።

2. DHHS ጋር በመተባበር፣ MCPS የሰነድ አያያዝ ሂደቶችን ያዘጋጃል –

   a) ቦታዎችን እና አገልግሎቱ የሚያበቃበትን ቀን ጨምሮ የናሎክሰን/naloxone ክምችት፣

b) በበቂ መጠን መኖሩን፣ እና ጥቅም ላይ የሚውልበት ጊዜ አለማብቃቱን ለማረጋገጥ የተከማቸ መድኃኒት መደበኛ ቁጥጥር መደረግ አለበት፣

c) የመድኃኒት ክምችትን መተካት፣

d) የኢቨንተሪ ዝርዝር ሰነድ፣ እና

e) ራሳቸው ለሚወስዱት የተመደቡ ተቆጣጣሪ ግለሰቦች።

3. ርእሰ መምህራን፣ SCHN ጋር በመመካከር፣ ናሎክሶን ለማከማቸት ተስማሚ እና ስልታዊ ቦታዎችን ይለያሉ፣ በተጨማሪም በየትምህርት ቤቱ ህንፃ ውስጥ ካለው የትምህርት ቤት ጤና ክፍል (ለምሳሌ፦ ከሌሎች የድንገተኛ ህክምና መሳሪያዎች ወይም አቅርቦቶች ጋር)

C. ከመጠን በላይ የመውሰድ ጥርጣሬ ሲኖር የናሎክሶን የድንገተኛ ጊዜ አሰጣጥ

1. ኦፒዮይድ ከመጠን በላይ መውሰድን የሚያስጠረጥሩ ምልክቶች

አንድ ሰው ከሚከተሉት ምልክቶች ጋር በተዛመደ ኦፒዮይድ ከመጠን በላይ መውሰዱ(ዷ) ከታመነ ናሎክሶን መሰጠት አለበት፥ እና 911 ወዲያውኑ ይደውሉ።

a) ራስን መሳት፣

b) በጣም ትንንሽ ተማሪዎች፣

c) በጣም ይንቀረፈፋሉ፣ ግልብ ይሆናሉ ወይም መተንፈስ ያቅታቸዋል፣

d) ማስታወክ/ማስመለስ፣

e) መናገር አለመቻል፣

f) ደካማ ወይም መደበኛ ያልሆነ የልብ ምት፣

g) የክንድ ወይም የእግር መዛል፣

h) የገረጣ ወይም የተነፋፋ ቆዳ፣ እና/ወይም

i) ሐምራዊ ከንፈር ወይም ጥፍር።

2. ሰዎች

a) ኦፒዮይድ ከመጠን በላይ መውሰድ ከተጠረጠረ እና ሀኪም ወይም የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ሰጪዎች ወዲያውኑ የማይገኙ ከሆነ፣ SCHN ወይም የትምህርት ቤት የጤና ክፍል ቴክኒሻን (SHRT) ከመጠን በላይ ኦፒዮይድ የመውሰድ ችግር ላለበት ሰው ናሎክሶን/naloxone መስጠት አለባቸው።

b) ት/ቤቱ የተመደበ SCHN ከሌለው ወይም SCHN እና SHRT የማይገኙ ከሆነ፥ የሰለጠነ በጎ ፈቃደኛ ናሎክሶን ሊሰጥ ይችላል።

3. ሰነድ

    a) SCHN ናሎክሶን የተሰጠበትን ሰነድ ከርእሰ መምህር ጋር በመነጋገር ይሞላል።

    b) ሁሉም የናሎክሶን አሰጣጥ MCPS ደንብ COB-RA፣ ያጋጠመ ክስተት ዘገባ፣ እና በሜሪላንድ የጤና ማምሪያ መመሪያዎች መሰረት ሪፖርት ይደረጋሉ።

4. የመድኃኒት ክምችት መተካት/መሙላት

    MCPS እና DHHS ያገለገሉ ናሎክሰን እቃዎችን በፍጥነት የመተካት ሥራ በትብብር ይሰራሉ።

D. ለወላጅ/ለሞግዚት ማሳወቅ

1. በማንኛውም ጊዜ ናሎክሶን MCPS ንብረት ውስጥ ኦፒዮይድ ከመጠን በላይ በመውሰድ ለተጠረጠረ(ች) ተማሪ በተሰጠበት ጊዜ፣ ናሎክሰን ለተሰጠው/ለተሰጣት ተማሪ ወላጆች/አሳዳጊዎች ወዲያውኑ እንዲያውቁት ይደረጋል።

2. MCPS ስለዚህ ደንብ በየአመቱ ለወላጆች/አሳዳጊዎች የማሳወቅ ስልት በማዘጋጀት ተግባራዊ ያደርጋል።

E. በግል የሚወሰድ ናሎክሶን/Naloxone

1. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች በተናጥል ስልጠና ለመውሰድ እና ናሎክሰን በ MCPS ንብረት ውስጥ ለመያዝ መምረጥ ይችላሉ። ሰራተኞች MCPS ደንብ፣ EBJ-RA፣ የአደጋ ጊዜ እንክብካቤ እና በት/ቤቶች የመጀመሪያ እርዳታ አሰጣጥ መመሪያ ላይ በተገለጸው መሰረት ለታመሙ እና/ወይም ለተጎዱ ተማሪዎች የድንገተኛ ህክምና እርዳታ ሂደቶችን የሚዘረዝር የት/ቤታቸውን የአደጋ ጊዜ እንክብካቤ እቅድ ማወቅ አለባቸው።

2. ናሎክሰን MCPS ንብረት ውስጥ እና በትምህርት ቤት ስፖንሰር የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ወቅት ይዘው የተገኙ ተማሪዎች ናሎክሰን በመያዛቸውም ምክንያት ብቻ የቅጣት እርምጃ አይወሰድባቸውም።

3. ኦፒዮይድ ከመጠን በላይ የመውሰድ ጥርጣሬ ካለ፥ ተማሪዎች DHHS ወይም MCPS ሰራተኞችን እና/ወይም 911 እርዳታ ለማግኘት እንዲያነጋግሩ በጥብቅ ይበረታታሉ።

F. ተገቢ የሆነ እና ነፃ ድጋፍ ወይም እርዳታ

በሜሪላንድ ህግ እንደተደነገገው፣ ድንገተኛ አደጋ በሚደርስበት ቦታ ለተጎጂው ሰው እርዳታ ወይም የህክምና እርዳታ የሚሰጥ ግለሰብ ለማንኛውም ድርጊት ወይም ግድፈት የፍትሐ ብሔር ህግ ተጠያቂ አይሆንም–

1. ድጋፍ ወይም እርዳታ መሰጠት ያለበት ተገቢ በሆነ መንገድ ከሆነ

2. ድጋፍ ወይም እርዳታው ያለ ክፍያ ወይም ሌላ ማካካሻ የሚሰጥ ነው፣ እና

3. በሜሪላንድ ስቴት የህክምና አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ ያለው ወይም የምስክር ወረቀት ያለው ሰው ሀላፊነቱን ለመውሰድ ሲመጣ ለተጎጂው(ዋ) እንክብካቤ ሲያደርግ የነበረ(ች)ው ሰው ርዳታ መስጠቱን ለህክምና ባለሙያው ይተዋል/ያቋርጣል።

4. በትምህርት ቤት ባለው ናሎክሶንን ምትክ በቅን ልቦና በግል የሚሰጡ ሰዎች በሜሪላንድ ኮድ፣ አጠቃላይ-ጤና አንቀጽ §13-3108 (a) መሠረት በበሽታ መከላከል ጥበቃ መመሪያ ይሸፈናሉ።

G. ተጨማሪ መረጃ

በአደንዛዥ እጽ አጠቃቀም እርዳታ ስለሚፈልጉ ተማሪዎች ወይም ሰራተኞች ድጋፍ የቦርድ ፖሊሲ IGN፣ አልኮል፣ ትምባሆ፣ እና ሌሎች የአደንዛዥ ዕፅ አላግባብ መጠቀምን በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ፣ እና MCPS ደንብ IGO-RA፣ ተማሪዎችን የሚመለከቱ የአልኮል፣ የትምባሆ እና ሌሎች የአደንዛዥ ዕፅ አላግባብ የመጠቀም ክስተቶች ተጨማሪ መመሪያ።

**ተዛማጅ ምንጮች:** Annotated Code of Maryland, Courts and Judicial Proceedings Article §5-518 and §5-522(b), Education Article, §4-106, §7-426 et seq, and §7-426.5, Health-General Article §5-603, §5-629, §13-3108(a); Code of Maryland Regulations 13A.05.05.05-.15

**የደንቡ ታሪክ:** አዲስ ደንብ፣ ሜይ 1, 2023።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (የግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግሥት ጥበቃ የተደረገላቸው ወይም ትስስር ያላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ ሲደረግ የቆየ ጥረትን ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Montgomery County Board of Education Policy ACA" ይመልከቱ፡- ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል "Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ሴት ልጅ ስካውት እና ለሌሎች የወጣት ቡድኖች እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።**

<table>
<tr><th>MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*</th><th>MCPS ሰራተኛ ላይ መድሎዎ ሲፈፀም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*</th></tr>
<tr><td>Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>SWC@mcpsmd.org</td><td>Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td>በ1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ</td><td>በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ</td></tr>
<tr><td>Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Well-being<br>Office of Well-being, Learning and Achievement<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-5630<br>504@mcpsmd.org</td><td>ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td colspan="2">"Title IX" ድንጋጌ መሠረት፥ ስለ ጾታዊ መድሎአዊነት በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች* ላይ ስለሚፈጸምባቸው ጾታዊ ጥቃቶች ጭምር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች</td></tr>
<tr><td colspan="2">Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>TitleIX@mcpsmd.org</td></tr>
</table>

**ስለ መድሎአዊነት ቅሬታ/አቤቱታ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡- U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

**ይህ ማስታወቂያ ከተሻሻለው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ህግ ጋር የተሳለጠ ነው።

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቅርጸት ለማግኘት ከተጠየቀ፥ በ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት፣ MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay)፣ ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ወይም ንግግር ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በዚህ ኤሜይል ወይም ስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org